★ዴሞክራሲያ★

ዴሞክራሲያ ቅጽ 37 ቁጥር 6 ሐምሌ/ነሐሴ 2004 ዓ.ም

# የት ደርሰናል?

***ያለፈውን ማስታወስ ለዛሬም የማይናቅ ጠቀሜታ አለው ፤ ይህን ብለን ነበር ለማለት ሳይሆን ተመክሮን ሚዛን ለመስጠትና ትምህርትንም ለመቅሰም በሚል ነው።***

> *" የካቲት በየካቲት ሲተካ፤ ያንን በሕዝብ ትግልና መስዋዕትነት ህያው የሆነን የካቲት 66 ስንዘክር የት ደርሰናል ብሎ መጠየቁ ፤ ሀገሪቷን ያራሰው የዜጋ ደም ምን አተረፈልን ብሎ መመራመሩ የግድ እንደሆነብን አለ። ሰብዕናውንና መብቱን የሚያከብርለት ሥርዓት ሲሻ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያካሄደው መራራ ትግልና የከፈለው መስዋዕትነት በታሪክ የተመዘገበ ሲሆን በተደጋጋሚ የትግሉን ፍሬ እየተነጠቀ፤ የጠላው እየቀጠለበት፤ ጨቋኝና አፋኝ ገዢዎች እየተፈራረቁበት ፍዳውን መቁጠር ተገዷል። የት ደርሰናል ስንል ዛሬ ያለንበትን ከመጣንበት ብቻ ሳይሆን ከተመኘነውና አልመነው ከነበረው አኳያም ፤ በተለይም ውድ ወንድሞቻችንና እህቶታችን ደማችውን ካፈሰሱለት ዓላማና ግብ አኳያ ማየታችን አይቀሬ ነው።*
>
> *(ዴሞክራሲያ-- የካቲት 1998)*

**ዛሬ የኢሕአፓን የምስረታ አርባኛ ዓመት፤ ይፋ የወጣበትንና የታወጀበትን (ነሐሴ 26) ሰላሳ ሰባተኛ ዓመት ስናከብር ከቀጠለው ሕዝባዊ ትግል አንፃርና ምን ማድረግ አለብን? ምን ማድረግ ይገባናል? ለሚሉት ጥያቄዎችም መልስ ለመስጠት እንችል ዘንድ የት ደርሰናል የሚለውን አለምንም ብዥታና ውዠንብር በጥሞና ማጤን፣ መመርመር፣ መገንዘብ ይኖርብናል። ከሞቱ በኋላ ማልቀስ ድንጋይ መንከስ የተባለው እንዳይተረትብንም ይረዳል።**

**የት ደርሰናል? ላለፉት ሃያ ዓመታት የኢትዮጵያ መሠረታዊ የፖለቲካና ኤኮኖሚያዊ ገፅታ የተሳለው በነበረውና ዛሬም ባለው መሠረታዊ ቅራኔ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ይህ መሠረታዊ ቅራኔ የለም ከተባለ ወይም ከተካደ ለችግሮች የሚሰጠውም መፍትሔ የተለየ ይሆናል። የወያኔ መንጋ ለሥልጣን ከበቃ ጀምሮ የህገራችን መሠረታዊ ቅራኔ በወያኔ አገዛዝና በመላው ሕዝብ መህል ያለ ነው። ይህ ምን ማለት ነው? ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለው ዋናና የከረረው ቅራኔ የርስ በርስ ሳይሆን ከወያኔ አገዛዝ ጋር ያለው ነው። በሃይማኖት፣ በብሔረሰብ፣ በአካባቢ፣ ...ወዘተ**

ወያኔ ሕዝብን እርስ በርሱ ለማናከስና ለማጋጨት ጥረት አድርጎ በአንዳንዱ ላይ ጉዳትን ቢያደርስም ዕቅዱ አልተሳካለትም። የሙስሊም ኢትዮጵያውንን ፍትሐዊ ተቃውሞ አጣሞ ሊያቀርብና ክርስቲያኑን ሊያስፈራራ፣ ሊያስጨንቅ የሞከረውም ፍሬ አልባ ሆኗል። ዘረኛው አገዛዝ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ በሕዝብ ተጠልቷል፤ የሕዝብ ተቃውሞም ከቀን ወደ ቀን እየጎለበተ ነው። ለውጥ አዘል ቀውስ ዳምኖ ባለበት በአሁኑ ጊዜ ገዢው ክፍል ባለፈው መንገድ ሊገዛ ወይም ሊቀጥል እያቃተው መምጣቱ የሚታይ ነው። ይህ ሁኔታ እንደተለመደው ከሕዝብ አልገዛም ባይነት ጋር ሲዳበል ደግሞ ዘላቂና ለሕዝብ ሊበጅና ሊጠቅም የሚችል ለውጥን መውለዱ አይቀሬ ነው። የአገዛዙ አምባገነናዊ ቁንጮ በግሉ፣ ሥልጣኑ አከትመ አላከተመ የሥርዓቱ መሸርሸርና መቃወስ መሠረታዊና ያለም የሚታይም ነው። የወያኔ አገዛዝ ከነፈሰበት በላይ ስንጥቅጥቅ እያለና እራሱንም በሙስናና በሥልጣን ሽኩቻ እየጎሸመ ነው። አሁንም ግን ይህ ሐቅ ለውጥን በራሱ ሊወልድ የሚችል አይደለም። አገዛዙ በጋራ ያለበትን የውድቀት አደጋ ተገንዝቦና በተለይም ተከታዮቹን በታልቃላችሁ ፍርሀት ቀይዶ መውጫ ቀዳዳውን መፈለግ ብቻ ሳይሆን ማግኘትም ይችላል። በ1997 ምርጫ ጊዜ ያየነው ሐቅ ነው--አገዛዙ በባዕዳን እርዳታና በወኔ ቢሶች ትብብር በርካታ ወገኖቻችንን ገድሎና አስሮ በሥልጣኑ ሊቀጥል ችሏል ።

የገዢው ክፍል ቀውስ የመሠረታዊ ለውጥን በር እንዲከፍት ከተፈለገ ሕዝብም ባለፈው መንገድ፤ መጨቆን መገዛት በቃኝ እምቢኝ፤ አሻፈረኝ ብሎ ለለውጥ መነሳት አለበት። ይህ አቅዋም ዛሬ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ እየታየና እየጨመረ የመጣ ቢሆንም ገዢው ክፍል የወረወረውን ጋሬጣ ሁሉ የሕዝብ ጎራ ማስወገድ ገና አልቻለም። ይህ መሠረታዊ ድክመት ደግሞ ድርጅትን ወይም የመደራጀት ድክመትን ይመለከታል። ድርጅት ሁላችንም እንደምናወቀውና እያየንም እንዳለው በዘመነ ወያኔ እንደ አሸን ፈልቷል፤ እንደ አሸዋም ተዘርቷል። የይዘት ጥያቄን ገና ሳናነሳ ግን ስንቱስ በርግጥ ህልወና ያለው ቡድን ነው ብለን ብንጠይቅ መልሱ የሚያኮራ አለመሆኑን ሳንደብቅ መቀበል አለብን። ወያኔ ለሥልጣን በበቃ ማግስት ስንቱ የብሔረሰብ "ድርጅት" መሥራችና ባለቤት ሆኖ መኮልኮሉን ዛሬም አንረሳውም። ስንቱ ለሕዝብ ቆመ? ስንቱ ተለጣፊ ሆኖ ተነነ? ስንቱ የዚያ በወያኔ የተቀነባበረው የሽግግር ትያትር አጃቢ ሆኖ ሳይውል ሳያድር በሕዝብ ተጋልጦ ተጣለ? መልሱ ለሕዝብ የተሰወረ አይደለም።

ምን ያህል የሕዝብ ንዴትና ቁጣ ቢበረታ በራሱ ወላፈን ብቻ አስከፊ አገዛዝን ማስወገድ አይችልም። እንቅስቃሴና አመፅ መኖር አለበት። ለዚህ አማራጭ የለም ከቶ። እግር ለጠጠር ደረት ለጦር ብሎ የሚነሳ ሕዝብ ያስፈልጋል። ይጨርሱናል ብለው የሚርዱ፤ መሰዋዕትነት ለመክፈል ቅንጣትም ዝግጁ ያልሆኑ ፤ ከገዢው ክፍል ጋር በጥቅም የተሳሰሩ የሕዝብ ትግል መሪዎች ነን ብለው መድረክ ከያዙ፤ ዋ ለዚያ መከራ ለሚያይ ሕዝብ ማለቱ ይመጣል። ሕዝብ ካልተደራጀና የሚመራው ወይም የሚመሩት ቆራጥና ሕዝባዊ የሆኑ ድርጅቶችን ካላገኘ ትግሉ--ያውም ተሰበጣጥሮ--ከድል በር አይደርስም። ወያኔ የረጨው የክፍፍል መርዝ በጠበቀው ደረጃ ሀገሪቷን ባያጠፋም ብዙዎችን

መበከሉና የሕዝብን የጋራ ክንድ ማዛሉ የሚታወቅ ነው:: ወያኔ የትግራይን ሕዝብ ወኪልህ ነኝ በሚል የለፈፈው ዛሬ ሁሉንም ባይሆን በመጠኑም ቢሆን አልበከለም፤ አላደናገረም፤ ከሕዝብ አላጣላም ማለት አንችልም:: በዚህ መስክ ለውጥ እየታየ ቢሆንም የወያኔ የአፈና ተቋሞችና መሣሪያዎች አሁንም ቢሆን በትግራይ ተወላጆች የተያዙ ከመሆናቸውም በላይ መለስን ተቃወምን የሚሉትም የቀድሞ ወያኔዎችም ቢሆኑ የትግራይ የበላይነት የሚሉትን በመለስ--አልባ ወያኔያዊ አገዛዝ በባዕዳን ድጋፍና በተለመዱት አድርባዮች አጀብ ሊጭኑብን ተዘጋጅተዋል:: ለማንኛውም የባዕዳንና የሥልጣን ጥመኞቹ ዕቅድ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተቃረነ ነውና የነገን ቁልፍ ባዕዳንና አምባገንኖች አልያዙትም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም ቢሆን የሀገሩን ዕጣ ፈንታ ሊወስን የሚችልበት ሁኔታ በእጁ አለ ::

ይህን እያልን ግን ከታሪካችን እንደምንረዳው ሕዝባችን ያጋጠመውን የዴሞክራሲያዊ ወይም የጠቃሚ ለውጥ ዕድል ሁሌም ያከሸፉት የሥልጣን ጥም የተጠናወታቸውና ለጥቅም ያደሩ እንዲሁም ባዕዳን ናቸውና ይህ እንዳይደገም መታገል የዜጎች ግዴታ ይሆናል:: ከጥንት ጀምሮ በተግባር ሲውል ያየነው የኢትዮጵያን ብሩህ ተስፋ የሚያፍኑት ባዕዳንና ቅጥረኞቻቸው መሆናቸውን ነው:: ራቅ ያለውን ማስታወሱ ለአዲሱ ትውልድ የሚጠቅም ቢሆንም ዝርዝሩ በርካታ ስለሆነ በዚህ እንተወውና የቅርቡን ስናስታውስ በ1997-ሉ ምርጫ ሕዝብ ለወሳኝ ሙት ከተማ አድማ ተዘጋጅቶ በነበረበት ሁኔታ የሕዝብ መሪ ነን ያሉ በባዕዳን ትእዛዝ አድማውን እንዳከሸፉት ታዝበናል:: የሕዝብን ከፍተኛ ድል ነጥቀው ከወያኔው መሪ ጋር ሊደራደሩ የቋመጡት ለባዕዳን ፍላጎት ተገዢ ሆነው ሀገራችንን ጎድተዋል:: ዛሬም አመቺውን ሁኔታ አከርካሪውን ሰብረው ለወያኔና ባዕዳን ሰለባ ሊያደርጉት የሚፈልጉ ክፍሎች በዚያም በዚህም ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋልና ተጨባጩን ሁኔታ ሕዝብ ይህን አውቆ አመፁን እንዲያፋፍም የግድ የላል:: የት ደርሰናል ስንል ለውጥን ያረገዘ ማጠፊያ ላይ የሚል ነው:: የምንወስደው አቅጣጫና ውሳኔ ወይ ለነፃነታችን ያበቃናል ወይም ለዳግማዊ ወያኔ አገዛዝ ፤ ለሁለተኛ ዙር 1983 ይዳርገናል:: ትግላችን ውጤቱን ይወስናል ::

በዚህ ትንቅንቅ ውስጥ የኢሕአፓ ቦታ-- ዛሬም እንደ ትላንት--ከሕዝብና ከሀገር ጥቅም ጎን ነው:: ለባዕድ አልሰገደም፤ ከወያኔ ጋር ተሞዳምዶ ሚኒስቴር ከንቲባ አርጉኝ አላለም ስለዚህም “አክራሪ ነው”፤ ... ወዘተ ለሚሉት ጆሮን የሚሰጥ አልነበረም፤ ዛሬም አይደለም:: ሕዝብን ያታገለን ደርጅት፣ ሕዝብን አስጨረሰ ብለው ማውገዝ የሚቀናቸው፤ ዛሬ እንደ ግብፅ፣ ቱኒዝያ፣ ሊቢያ፣ ... ወዘተ ሕዝብ በ.ነሳሳ ወያኔ ይጨርሰናልና ፀጥ ብለን እንገዛ፤ ሌላ ምርጫ እንጠብቅ ብለው የሚሰብኩትንም ኢሕአፓ ማጋለጥ ብቻ ሳይሆን ከሀዲዎቹ ከባዕድ ጋር ያቀዱት እንዳይሳካ ባለው ኃይል ሁሉ ይታገላል:: የወያኔ አገዛዝ በአዲስ ጭምብል እንዳይቀጥልም ትግሉን የሚቀጥል ይሆናል::

የት ደርሰናል ስንልም የጠላትን ዜዴና ስስ ብልትም የምናውቅበት ደረጃ ላይ ከመሆናችን በተጨማሪ የሕዝብም ጎራ ያለውን ድክመትና ጥንካሬ የምንገነዘብበት ቦታ ላይ ነን:: የወያኔን አገዛዝ ጠላት አትበሉ የሚሉ ዛሬም - ከሀያ ዓመታት መከራ በኋላም - መኖራቸው ራሱ የችግራችንን ደረጃ

ገላጭ ነው:: ጠላት--የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያና የሕዝብ ጠላት ነውና--ዋና ጥንካሬው የአፈና መዋቅሮችን መቆጣጠር መቻሉ ነው:: የፀጥታ ኃይሉ፣ የጦር ኃይሉ፣ ቢሮክራሲው፣ ... ወዘተ በወያኔ አገዛዝ ሥር ነው:: የወያኔ ሌላ (ጥንካሬ እንበለውና) ሕዝብን በብሔረሰብና በሃይማኖት ደረጃ ለመከፋፈል ከመጣ እስካሁን ሳያሰልስ መሥራቱ ነው:: የለውጥ ኃይል የሆነው ወጣት በተለይ የዚህ ሰለባ መሆኑ የሚካድ አይደለም:: የሀገራችን መሬት ለሱዳን ሲሰጥ የነበረው ተቃውሞም ይህን ያህል አልነበረም:: የተጠበቀው አመፅ አልተከሰተም:: ቀቢፀ ተስፋን መጋለቢያ ሜዳ ለመስጠት ሳይሆን ድክመት ጥንካሬያችንን ለማወቅ ነውና የሀገራችን ለም መሬት ለባዕዳን ሲሰጥም እርምጃ መውሰድ ላይ ድክመቱ ዛሬም ያለ ነው:: የሕዝብ ጠንካራ ጎን ደግሞ የወያኔን መርዝ ተቋቁሞ ሀገሩን ለማዳን ዛሬም ሊቆም የሚችልበትን ሁኔታ ማሳየቱ ነው:: የሕዝብን ትግል ከማጠናከር አንፃርም--በተለይ ድርጅታዊ ዝግጁነትና ብቃትን በተመለከተ--አያሌ ተመክሮ ተገብይቷል:: በወያኔ በሃይማኖቱም ሆነ በጎሳው መስክ የተደረገው የጥላቻ መርዝን ተቋቁሞ እስካሁን እርስ በርሱ ችግሩን እየፈታ መቀጠሉና የወያኔን ሴራ ማክሸፉም የሕዝባችን ሌላው ጥንካሬው ነው:: ስህተትን መድገም፤ ታሪክ ያዋረዳቸውን አድርባዮች ማስተናገድ፣ አሁንም የለብንም::

በፖለቲካው ታሪካዊ ሂደት ኢሕአፓ በየሽግግሩ አጋጣሚ ለሀገርና ለሕዝብ የሚበጅን አማራጭና መንገድ መጠቆሙ የሚታወቅ ነው:: በአፄው ውደቀት ጊዜ፣ ኢሕአፓ በሰላምና በዴሞክራሲ መታገል ከተቻለ ዝግጁ ነን ብሎ ነበር:: መልሱ አፈናና ሽብር ሆነ:: የግንባር ጥሪ መሰል ሲቀርብም በይፋ በልሳኑ በዴሞክራሲያ አማካኝነት ማንኛውም ሕብረት ሆነ የሽግግር ሂደት ሁሉን አቀፍ መሆን አለበት ሲል ኢሕአፓ አቅዋሙን ገልፆ ነበር:: ገና ከደርግ ዘመን ጠዋት ጀምሮ፣ ኢሕአፓ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም ያለው፤ ሰፊ ሕዘባዊ መሠረት ያለው መንግሥት የኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ያረጋግጣል በሚል ነበር:: ይህን ግን ወታደራዊ አምባገነኖች ተቃውመውና ሕዝብን ፈጅተው አደናቅፈውታል:: በ1997ም ኢሕአፓ በህብረት አማካይነት የሙት ከተማ አድማን ፅንስ ሀሳብ አቅርቦ ለአመረረ ትግል ያደረገው ጥረት በባእዳንና በአንዳንድ ግለሰቦች ሻጥር ከሽፏል:: ዛሬም የኢሕአፓ መልዕክትና አማራጭ ለወያኔ አገዛዝ መወገድ ሕዝባዊ አመፅን እናፋፍም የሚል እንጂ ከወያኔዎችና ከባዕዳን ተቃቅፈን፤ ሕዝባዊ አመፅን፣ ጎጂና አጥፊ ነው ብለን እንበርከክ የሚል አሳፋሪ አቅዋም አይደለም::

ዛሬም ይህ ነው ሊባል የሚችል ህልውና ያላቸው ተቃዋሚ ሀይሎች የፈጠሩት ህብረት በሌለበት በሩቅ ርቀትና በወረቀት ብቻ ህብረት ያለ አስመስሎ ማቅረቡ ወያኔን የሚያባባና የሚያደናግጥ ሳይሆን ሕዝብን የሚያደናግር በመሆኑ ኢሕአፓ በዚህ ዓይነቱ ቧልት እንደማይሳተፍ እቋሙን አስረግጦ፤ ይልቁንስ በትግሉ ሜዳ በሀገራችን እንተባባር የሚለውን ጥሪ አስተጋብቷል:: ይህ ገንቢ አቅዋም ምላሽ አላገኘም:: ኢሕአፓ ከአፄው ዘመን ጀምሮ በህብረት ለመታገል ያደረጋቸው ሙከራዎች፤ ያገኛቸው ውጤቶችና የደረሱበትም ችግሮች በታሪክ የተመዘገቡ ናቸው:: ደሙን ካፈሰሱት ሳይቀር ለሀገር ብሎ ህብረትን መሥርቶ ቁጭቱን አፍኗል:: ለኢዴኃቅም ሆነ ለኢዴኃህ

ምስረታ ኢሕአፓ ያደረገውን አስተዋፅኦ ሁሉም የሚያውቀው ነው:: እነዚህ ሁሉ ሙከራዎች ለትግሉ ጠቃሚ አስተዋፅዖ አድርገውና ድክመትንም እንፀባርቀው አልፈዋል:: ከዚህ ተመክሮና መማር የሚጠበቅ ነው:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ ዛሬም ስምን እየቀያየሩ ህብረት ወይም ጥምረት ነኝ ባይ እንቅስቃሴ መዳከሩ ፍሬ የለውም፤ አይኖረውም:: በዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያስፈልገው ህብረት በተጨባጭ ትግል ላይ የተመሠረተ መሆኑ ላይ ነው:: ሀገር የማዳኑ ተልዕኮ የሚጠይቀው አመራር ያመረረ ፀረ-ወያኔነት ነው እንጂ ሥልጡን ፖለቲካን ወይም ሌላ ማጠየቂያን ባቀፈ ፅንሰ ሀሳብ ዘላቂውን የሕዝብ ጥቅም አሳልፎ በመስጠት ሽብረክ ጎንበስ ማለትን የሚያስተናግድ ሂደት አይደለም::

ወያኔ ሕዝብን ከፋፍሎ ለመቀጠል ሳይታክት እየሠራ ነው:: የአፈና መዋቅሮችን ተቀቆጣጥሩሯል:: የአሜሪካንን ድጋፍም በሎሌነቱ አግኝቷል:: በተፃራሪው ግን የሕዝብ ድጋፍ የለውም፤ ቀውስ ውስጥ ገብቷል:: ሕዝብም ጠልቶት ለውድቀቱ እየጣረ ነው:: ይህን ጥረት ጥንካሬ መስጠት ያስፈልጋል:: ለሀገር የሚበጅ የሽግግር ሙከራ የምንለው በወያኔ ሥር ወይም ወያኔን አቅፎ የሚካሄድ ሊሆን አይችልም:: በነሐሴ 1995 በወጣው የዴሞክራሲያ ዕትም "ነገን ለመጨበጥ ዛሬ መዘጋጀት--ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ጥያቄ" በሚል ርዕስ በዚህ አቢይ ጉዳይ ላይ ሰፊ ገለፃ ኢሕአፓ ሰጥቶ እንደነበር ያስታውሷል:: ኢትዮጵያን ሸምቅቆ ይዞ ያሰቃያት አምባገነንነት ለአንዴም ለሁሌም እንዲያከትም ከተፈለገ ፤ ሰላምና ዕድገት በሀገሪቷ እንዲመጣ ከታሰበ፤ ሕዝቧ በእኩልነት፣ በፍቅርና በአንድነት በዴሞክራሲ ጥላ ሥር እንዲሰባሰብ ከፈለግን ሁሉን አቀፍ ዴሞክራሲያዊ ሽግግርን ማረጋገጥ መቻል አለብን:: ያለውን ፀረ ሕዝብ ሥርዓት ዳግም በአድርባዮች ደግፎና ጠጋግኖ ጭቆናን በመቀጠል ግን መሆን የለበትም:: ኢትዮጵያ ሀገራችን ሉዓላዊነቷን አጥታ፤ የባዕድ ጦር ሰፍሮባት፤ የባዕድ ጥቅም ለማሟላት ዜጎቿን አሳልፋ ሰጥታ በአፍሪካ አህጉርና በዓለምም ደረጃ ማፈሪያ እየሆነች ያለችበት ሁኔታም አክትሞ ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷን ማስከበር አለባት እንጂ አንደ 1983 ዕጣ ክፍሏን ባዕዳን እንዲወስኑ መተው የለባትም:: ከሁሉም በላይ ግን የወያኔ ፀረ ኢትዮጵያ አገዛዝ ከሥረ መሠረቱ ተነቅሎ መወገድ እንዳለበት ማወቅ፤ መገንዘብና በትግልም ዕውን ማድረግ ያስፈልጋል::

የት ደርሰናል ስንል፤ ይህ ካላይ የተዘረዘረውን ሁሉ አካቶ መዳረሻችንን እነሆ ይለናል:: ለሀገራችን በአፍ ሳይሆን በገቢር መሰዋት እንዳለብን የሚያሳይ ቦታ ላይ ደርሰናል:: ታሪካችን የምናድስበት ወቅት ላይ ደርሰናል:: በቃ አከተመ ፤ ደቀቀ ወደመ ብለን የወያኔ አምባገነንነት አገዛዝ መቃብር ላይ የምንቧርቅበት ጊዜም አሁን ነውና ተነሱ ይለናል:: በኢትዮጵያ የነፃነትና የዴሞክራሲ ነጋሪት የሚጎሰምበትና የሰላምና ዕድገት ጥሩምባ የሚነፋበት፤ በዕኩልነት የአንድነት ምዕራፋችን በተጨባጭ መሠረቱ የሚጣልበት ጊዜ ላይ ደርሳችኋልም የሚለን ወቀት ላይ ነን:: ለዚህም በተግባርና በጠቃሚ መንገድ መተባበር እንደሚገባም ተጨባጭ ሁኔታው ይጠቁማል:: ሕዝብም በአድርባዮች የተቀማውን ድምፁንና ሚናውን ማስመለሻ ጊዜው ላይ ደርሷል::

**ነሐሴን በነሐሴ ብለን “የት ደርሰናል?” ለሚለው ጥያቄ በ1998 የሰጠነው መልስ ዛሬም ይሠራልና እንጥቀሰው--**

> ***“..ለዚህም ነው ሀገርን የማዳን ግዳጃችን ከዴሞክራሲ ሰንደቃችን ጋር አብሮ ተጣምሮ መጓዙን ማወቅና ማመን የሚገባን:: ከዚህ ቀደም እንዳልነውም ሀገር ከሕዝቦች ውጭ የምትገለፅ ግዑዝ ክስተት አይደለችምና ታሪኳን በደማቸው ፅፈው መስዋዕት ሆነው ሀያውነቷን ያረጋገጡላትን ልጆችዋን ጠረን ማሽተት፣ መልካቸውን መምሰል፣ የልብ ትርታቸውን ማጀብ፣ ራዕያቸውንም መሆን ይኖርባታል:: እያንዳንዱ ትውልድ፣ እያንዳንዱ ዜጋም ታሪክ የጣለበት ሀገራዊ ግዳጅ አለበት:: ከእኛ በፊት የነበሩት የሀገራቸውን ጥሪ ሰምተው በዱር በገደሉ ከግዙፍ ጠላቶች ጋር በመዋደቅ ሽንፈትና ክህደት ኢትዮጵያዊነትን አይገልጡትም ብለው ሀገር አቆይተውልን አልፈዋል:: ይህ ሊታለፍ የማይችል ከዕንቁ የከበረ የታሪክ ውርስ በእኛ ላይ ግዳጅ ስለሚጭን ወደ ሌላ ትውልድ የሚለጋ አይደለም:: ከሀገር በላይ ምንምና ማንም የለምና እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሀገሩን ለማዳን ዝግጁ ሆኖ በተጨባጭ ትግሉ ተሳታፊ እንዲሆን ከሚጠበቅበት ሁኔታ ላይ ነን” ::***

**ዛሬም ጥሪው ተነሱ ታገሉ የሚል ነው:: የወያኔን ቀውስ ለኢትዮጵያ ስርየትን ለሚያመጣ መሠረታዊ ለውጥ እንጠቀምበት:: ይህን ዓላማ ማደናቀፍ የታሪክም የትውልድም ተጠያቂነትን ያስከትላል::**

**በተባበረና ሥር ነቀል ትግላችን የዘረኛውን ወያኔ አምባገነንነት እናቸንፋለን !**
**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል !!**